# ምዕራፍ አራት

## ሥነ ውበታዊ ዕሴት (ዋጋ) (20ክ/ጊዜ )

### መግቢያ

በዚህ በምዕራፍ አራት ላይ ትኩረት የተደረገው የአንድን ነገር በተለይ የውዝዋዝ የትያትርና የሙዚቃ ጥበባት መጠቀም ያለው ስነ-ውበታዊ ዋጋ /እሴት ምን እንደሆነ እና የሙዚቃ፣ የትያትር፣ የውዝዋዜ አንድነትና ልዩነት ላይ ትኩረት በማድረግ ለማስቀመጥ የተሞከረበት እና የዕይታ ጥበብና የዕደ ትበባት አስፈላጊነት፣ አካላዊ ጥቅሞችና የዕይታ ጥበባት ትምህርት የማስታወስ ችሎታ ያሻሽላል የሚሉት ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡

## 4.1 ያሙዚቃ ጥበብ ሃሳብን ከውዝዋዜና ከቲያትር ጥበባት ሐሳብ ጋር ያለውን ልዩነትና አንድነት መወያየት(3ክ/ጊዜ)

አላማው

የሙዚቃ ጥበብ ከሌሎች የጥበብ ሙያዎች ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት በሚገባ እንዲወያዩ ማድረግ ነው፡፡

የሚጠበቅ የመማር ውጤት፡
ይህን ክፍለ ትምህርት ተምረው ከአጠናቀቁ በኋላ
- የጥበብ እንድነትና ልዩነት በሚገባ ይረዳሉ፡፡
- የሙዚቃ ጥበባት የትያትር ጥበብን አንድነትና ልዩነት ይረዳሉ፡፡

አጠቃላይ የመማር ማስተማር ስልቶች

- በዝማሬ፣ በማህረሰብ ውስጥ የዕይታና አእደ ጥበባት አስፈላጊነትን እንዲረዱ በማድረግ

የመማርና ማስተማሪያ መሳሪዎች

- የምስል ማሳያና የድምፅ መስሚያ ግብዓቶች፤
- ለናሙና የሚሆኑ የዕደ ጥበብ ውጤቶችና ምስሎች፡፡

አጠቃላይ ምዘናና ግምገማ

- ምልከታ
- የግል ፅብረቃ
- የቡድን ፅብረቃ
- ግለ ማህደር

### 4.1.1 የውዝዋዜ ሃሳብን ከሙዚቃ ከትያትር ጥበባት ሃሳብ ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነትመወያየት
(3ክ/ጊዜ)

የውዝዋዜ ጥበብ ከመሰል የጥበብ ሙያዎች ጋር ያለው አንድነት በተመለከተ በዝርዝር ስንመለከተው ሃሳብን በፈጠራ ስራ የሚገልፅ መሆኑ ሲሆን ልዩነቱ በአካል እንቅስቃሴ ላይ ያተኮረና ስራው በቅመራ(Cerograph) መከወን መቻሉን መወያየት፡፡

የሙዚቃ ጥበብ ማህረሰቡ በጥበባዊ ፈጠራው በተለያዩ መንገዶች ነባራዊ ባህሉን፣ታሪኩን፣ማንነቱን የሚገልፅበትነው፡፡የሙዚቃ ጥበብ በህብረተሰብ ዘንድ ያለው ጉልህ እጅግ

አላማው

የውዝዋዜ ጥበብ ከሌሎች የጥበብ ሙያዎችጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት በሚገባ እንዲወያዩ ማድረግ ነው፡፡

የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ክፍለ ትምህርት ተምረው ከአጠናቀቁ ቦኃላ

- የውዝዋዜ ጥበብ ከሌሎች ሙያዎች ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት በሚገባ በመረዳት ያብራራሉ፡፡

አጠቃላይ የመማር ማስተማር ስልቶች

- በውዝዋዜ፣ በማህረሰብ ውስጥ የዕይታና አእደ ጥበባት አስፈላጊነትን እንዲረዱ በማድረግ

የመማርና ማስተማሪያ መሳሪዎች

- የምስል ማሳያና የድምፅ መስሚያ ግብዓቶች፤
- ለናሙና የሚሆኑ የዕደ ጥበብ ውጤቶችና ምስሎች፡፡

አጠቃላይ ምዘናና ግምገማ

- ምልከታ
- የግል ፅብረቃ
- የቡድን ፅብረቃ
- ግለ ማህደር

### 4.1.2 ልማዳዊየሃገረሰብ ውዝዋዜ

በአካባቢ ውስጥ የሚከናወኑ ማህበረሰቡን በጋራ የሚያስማሙ፤ በጋራ የሚከወኑ የድርጊት (ክዋኔ) ናቸው፡፡ ከነዚህ በጥቂቱ ዜማዎች (ሙዚቃዎች) ፣ ባህላዊ ውዝዋዜዎች ይጠቀሳሉ፡፡

መልመጃ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሱን ስጡ

1.ወዝዋዜ ልማዳዊ ክዋኔ ነው

2.ውዝዋዜ ለክብረ በዓላትና ፌስቲቫሎች አድማቂና ስሜት መግለጫ ነው

መልስ 1.እውነት  2. እውነት

### 4.1.3 የትያትር ሃሳብን ከሙዚቃና ከዕይታ ጥበባት ሃሳብ ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት መወያየት(3ክ/ጊዜ)

የትያትር ጥበብ ከመሰል የጥበብ ሙያዎች ጋር ያለው አንድነት በተመለከተ በዝርዝር ስንመለከተው ሃሳብን በፈጠራ ስራ የሚገልፅ መሆኑ ሲሆን ልዩነቱ በተውኔት መከወን መቻሉን መወያየት፡፡

አላማ

ትያትር በማህበረሰብ ውስጥ ያላቸውን ጥበባዊ ክዋኔዎች ጠቀሜታ በሚገባ እንዲረዱ ማስቻል ነው፡፡

የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ክፍለትምህርት ተምረው ከአጠናቀቁ ቦኃላ

- ስለ ትያትር በሚገባ ይረዳሉ

አጠቃላይ የመማር ማስተማር ስልቶች

- የቡድን ስራ
- ሰርቶ ማሰራት
- የተለማመዱትን ማሳየት
- ግልፅነት
- ማድመጥ

የመማር ማስተማር መሳሪያዎች

- የመለማመጃ ክፌልች፣
- የሙዚቃና የቪዲዮ ማጫወቻ፤
- የመዋቢያ ግብዐትና አልባሳት
- ምስሎች
- የምስሌ ማሳያና የዴምፅ መስሚያ ግብዓቶች፤
- ለናሙና የሚሆኑ የዕደ ጥበብ ውጤቶችና ምስልች

አጠቃላይ ምዘናና ግምገማ

- ምልከታ
- የግል ፅብረቃ
- የቡድን ፅብረቃ
- ግለ ማህደር

## 4.1.4 የዕይታ ጥበብ ሃሳብን ከሙዚቃ ከትያትር ጥበባት ሃሳብ ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት መወያየት(3ክ/ጊዜ)

የጥበብን በማህረሰቡ ውስጥ ክዋኔና ጠቀሜታ ስናነሳ ማህበረሰቡ በተለያዩ መንገዶች ባህሉን፣ ታሪኩን፣ ማንነቱንና ስሜቱን የሚገልፅባቸው እንዲሁም በጥበባዊ ፈጠራው ስራውን የሚያቀርብባቸው ናቸው። ጥበብ ለማህበረሰቡ ሁልንተናዊ ጠቀሜታ እንዳለው መዘንጋት የለበትም። በመሆኑም በዚህክፍል ስለ ሃገረሰባዊ ክውን ጥበባት፣ ሃገረሰባዊ ልማድና ቁሳዊ ባህል እናያለን።

አላማ

የዕይታና እደ ጥበባት በማህበረሰብ ውስጥ ያላቸውን ጥበባዊ ክዋኔዎች ጠቀሜታ በሚገባ እንዲረዱ ማስቻል ነው።

| |
|---|
| የሚጠበቁ ውጤቶች<br>ይህን ክፍለ ትምህርት ተምረው ከአጠናቀቁ በኂላ<br>• የጥበብ አስፈላጊነትን በሚገባ ይረዳሉ። |

የመማር ማስተማር መሳሪያዎች

- የመለማመጃ ክፍሎች፣
- ምስሎች
- የምስሌ ማሳያና የዴምፅ መስሚያ ግብዓቶች፤
- ለናሙና የሚሆኑ የዕደ ጥበብ ውጤቶችና ምስልች

አጠቃላይ ምዘናና ግምገማ

- ምልከታ
- የግል ፅብረቃ
- የቡድን ፅብረቃ
- ግለ ማህደር

አጠቃላይ የመማር ማስተማር ስልቶች

- በዝማሬ፣
- በማህበረሰብ ውስጥ የዕይታና እደ ጥበባት አስፈሊጊነት እንዱረደ ይደረጋል

የመማር መማር ማስተማሪያዎች

- የመለማመጃ ክፌልች፣
- የሙዙቃና የቪዱዮ ማጫወቻ፤
- የአካባቢ የምት የሙዙቃ መሣሪያዎች ወዘተ.፤
- ምስሎች
- የምስሌ ማሳያና የዴምፅ መስሚያ ግብዓቶች፤
- ለናሙና የሚሆኑ የዕደ ጥበብ ውጤቶችና ምስልች

አጠቃላይ ምዘናና ግምገማ

- ምልከታ
- የግል ፅብረቃ
- የቡድን ፅብረቃ
- ግለ ማህደር

የእየታ ጥበባት ለስነውበት አድናቆትን ከሚስጡት አንዱ እደጥበብ ፌጠራ በሙዚቃ የሀገር በቀል የባህል መሳሪያዎች የማህበረሰቡን ትውፊታዊ ማንነት ገላጭ ናቸው
ልማዳዊ የሃገረሰብ ክውን ጥበባት የምንላቸው ዜማዎች (ሙዚቃዎች) ፣ ባህላዊ ውዝዋዜዎች ፤የአነጋገር ልሳኖች፤ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፤የኑሮዘይቤዎች ፤ፀጉር አሰራር በማህበረሰብ አኗኗር ውስጥ የሚከወኑ ናቸው

ልማዳዊ ክዋኔዎች በማህበረሰቡ በየጊዜው እለት በእለት የሚተገበሩ ክወኔዎች የአንድነት ተግባቦትን የሚፈጥሩየጋራ እንቅስቃሴዎች ናቸው ። በእነዚህ ልማዶች ውስጥ በአለማዊውም ሆነ በመንፈሳዊ ህይወት የሚተገበሩ ናቸው።

የመልመጃ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።

1. ልማዳዊ የሆነ የውዝዋዜ ክዋኔ

ሀ. ቀረርቶ ለ. ንድፍ ሐ. እስክሰታ መ. ዳንስ

2. አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን ያዢ።

ሀ. ዘይቤ ለ. ምሳሌያዊ አነጋገር ሐ. ቅርፅ መ. ገላጭቃል ።

3. የክብረ በዓላትና ፌስቲቫሎች ገላጭ ያልሆነው

ሀ.በጋራ መሰባሰብ ለ. አብሮ መብላት ሐ. ግለኝነት መ. የማህበር ስራ

መልስ 1. ሐ 2.ሐ 3.ሐ

እዚህ በታች ለተጠየቁት ጥያቄዎቸወ አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ሐሰት በማለት መልስ ስጡ

1. የጥልፍ ስራ በልብስ ላይ ብቻ ያተኮረነው፡፡
2. የዶሮወጥ በባእላት እነደዚሁም አስፈላጊ በሆነ የክብር በአልላይ የሚቀርብ የምግብ አይነት ነው
3. የብረታ ብረት ስራ ሞፈር፤ ማረሻ ፤ ቀምበርን ያጠቃልላል

መልስ
1.ሀሰት 2.እውነት 3.ሀሰት

አላማ

ተማሪወች ስለማህበረሰባቸውና አገራቸው ልዩልዩ ጥበባዊ ክዋኔወችና ጠቀሜታቸው አወቀው እንዲያደንቁ ማስተማር ነው፡፡

ዝርዝር አላማዎች

- ሃገረሰባዊ ክውን ጥበባት
- ዘፈኖች
- ውዝዋዜወች
- ድራማወች
- ሃገረሰባዊ ልማዶች
- ባህላዊ ጨዋታወች
- ሃገረሰባዊ መድሃኒቶች
- ቁሳዊ ባህሎች
- የእጅ ስራውጤቶችን እንዲረዱ ማድረገግ ነው፡፡

ሃገረሰባዊ ክውን ጥበባት

በአንድ አገር ወይም አካባቢ ውስጥ የሚከናወኑ እና በውስጣቸው ባለው ይዘት እንዲሁም ማህበረሰቡንበጋራ የሚያስማሙ፤ በጋራ የሚከወኑ ከትውልድ ወደ ትውልድ በድርጊት (በክዋኔ) ወይም በመተወን የሚተላለፉ ናቸው። ሃገረሰባዊ ትውን ጥበባት ብለን በጥቅል ስም የምንጠራቸው ሃገረሰባዊ ሙዚቃዎችን፣ ሃገረሰባዊ ዳንሶችንና ሃገረሰባዊ ድራማወችን የሚያጠናውን ሙያና የሚጠኑትን ነገሮች ነው። ዳንስ፣ ሙዚቃና ድራማ በክዋኔ ውስጥ ለየብቻቸው የቆሙ ሳይሆኑ አንዱ በአንዱ ውስጥ የሚገኙና እርስበርስ የተሳሰሩ ናቸው።
ለምሳሌ፦ ሃገረሰባዊውን ዘፈን ብናነሳ ዜማ፣ ግጥም፣ ምልልስ፣ ገፀ- ባህርያትን፣ የቁጥር መመጣጠንን እና እስክስታን በአንድነት ሲከወኑ ታያላችሁ።

የመልመጃ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ ከሃገረሰባዊ ክውን ጥበባት ውስጥ የማናገኘው የቱን ነው?
ሀ. ሽለላ ለ. ስዕል ሐ. እስክስታ መ. መልስ የለም
2. ከሚከተሉት አንዱ ሃገረሰባዊ ጥበብን አይገልፅም።
ሀ. ታሪክን አይነግርም ለ. ሀዘንን ይገልፃል ሐ. ፈጠራን ያሳያል መ. ሁሉም መልስ ናቸው።
3. ሀገረሰባዊ ክውን ጥበባት የምንላቸው---
ሀ. ሙዚቃ ዳንስ እና ድራማን ይይዛሉ ለ. ባህላዊ ተግባራት ናቸው ሐ. ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋሉ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

ሀገረሰባዊ ልማዶች

በማህበረሰቡ ውስጥ ልማዳዊ በሆነ መንገድ በተደጋጋሚ የሚተገበሩ ክዋኔዎች ሲሆኑ ለማህበረሰቡአካላዊ ስነ-ልቦናዊና መንፈሳዊ (እምነታዊ) ጠቀሜታን ያስገኛሉ። በእነዚህ ልማዶች ውስጥ የተለያዩ ክብረበዓላትና ፌስቲቫሎች፣ መዝናኛዎችና ጨዋታዎች፣ ሃገረሰባዊ መድሃኒቶች፣ እንዲሁም ሀገረሰባዊ እምነቶች ተካተው ይገኛሉ። ለምሳሌ፦ ከሀገረሰባዊ ጨዋታወች ብናይ፡ የትግል (መጣጣል) ጨዋታን፣ የዱላ ምከታን፣ ብይ ጨዋታን፣ ገበጣ ጨዋታን፣ የዝላይ ጨዋታን፣ ገና ጨዋታን... ወዘተ. መጥቀስ ይቻላል።ሃገረሰባዊ እምነትን ስንመለከት፡ የተለያዩ ህልም አፈታቶችን፣ ከእድል ጋር የሚገናኙ እንደ የእጅ መዳፍ ማሳከክ፣ እግርን እንቅፋት ሲመታ፣ እና ምላስ ሲነከስ ሰው እያነሳኝ ነው ብሎ ማሰብን...ወዘተ. ይጠቀሳሉ።

ሃገረሰባዊ መድሃኒትን ብናይ ደግሞ፡ ከተለያዩ የእፅዋት ስራስሮችና ቅጠላቅጠሎች የሚቀመሙና ለተለያዩ በሽታወች እንደ ትኩሳት፣ ራስ ምታት፣ ምች፣ ጉንፋን ለመሳሰሉ በሽታዎችን … ወዘተ. ለማዳን ይጠቅማሉ፡፡
ተማሪዎች እናንተም ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ የተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎችን፣ እምነቶችንና ባህላወዊ መድሃኒቶችን ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ቁሳዊ ባህሎች የሰውልጅ አዕምሯዊ ፈጠራውን ተጠቅሞ ሃሳቡንና ስሜቱን እንዲሁም በቃላት ማይገልፃቸውን ጉዳዮች በአስገራሚና አስደማሚ መንገድ ቁሳቁሶችን በመስራትና ላያቸው ላይ በመቅረፅ የሚገልፅበት መንገድ ነው፡፡ በአንድ በተወሰነ ዘመን አንድ ህዝብ ያለውን ወይም የነበረውን እምነት፣ አስተሳሰብ፣ ባህል፣ እሴት፣ ስሜትና ተስፋ በቁሳዊ ባህሉ አማካኝነት በመቅረፅ ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላልፍበታል፡፡

በቁሳዊ ባህል ውስጥ ከሚጠቃለሉት ውስጥ ሃገረሰባዊ የእጅ ስራ፣ ሃገረሰባዊ ብረታብረት ስራ፣ የሸክላ ስራ፣ ሽመና፣ የቆዳ ስራ፣ ሃገረሰባዊ ቤት አሰራር፣ ድንጋይ ጠረባ፣ እንዲሁም የሃገረሰባዊ ምግብ አሰራር ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡- በዚህ ጥበብ ሀገራችን ውስጥ ከተላለፉልን ድንቅ ቅርሶች መካከል የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን፣ አልነጃሽ መስጊድ፣ ፋሲለደስ ቤተመንግስት፣ አክሱም ሀውልትና የጢያ ትክል ድንጋይ ከብዙ በትቂቱ ይጠቀሳሉ፡፡

የመልመጃ ጥያቄዎችየሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሃሰት በማለት መልሱ፡፡

1.የዶሮ ወጥ የኢትዮጵያ ባህላዊ ምግብ አይደለም፡፡
2. ባህላዊ መድሀኒቶች አብዛኛውን ጊዜ ከእፅዋቶች ይዘጋጃሉ፡፡
3. ጥቁር መልበስ በአብዛኛው የአገራችን አካባቢ ደስታን የምንገልፅበት ልማዳችን ነው፡፡
4. ጢያ ትክል ዲንጋይ በጉራጌ አካባቢ ይገኛል፡፡

የማስተማር ስልት

• ተማሪወች በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ፡፡
• በግል ከቤተሰቦቻቸው ስለመድሃኒቶች፣ ጨዋታወች፣ ቅርሶች፣ ምግብ አሰራሮች እንዲጠይቁ ማድረግ፡፡
• የጠየቁትን ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡
• ቅርብ ላይ ያሉ ታሪካዊ ቦታወችን ማስጎብኘት፡፡
• የጎበኙትን በፎቶ ግራፍና ቪዲዮ ካሜራ ቀርፀው እንዲያመጡ ማገዝ፡፡
• ልዩልዩ የአገር በቀል ክዋኔወችንና ቅርሶችን በቪዲዮ ማሳየት፡፡

የማስተማሪያ ቁሳቁሶች

- እስክርቢቶ
- ወረቀት
- ቪዲዮ ካሞራ
- ፕሮጀክተር
- ላብቶፕ

የመልመጃ ጥያቄዎች መልሰ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡ፡፡

1.ከሚከተሉት ውስጥ ከሃገረሰባዊ ክውን ጥበባት ውስጥ የማናገኘው የቱን ነው?ለ

ሀ. ሽለላ ለ. ስዕል ሐ. እስክስታ መ. መልስ የለም

2.ከሚከተሉት አንዱ ሃገረሰባዊ ጥበብን አይገልፅም፡፡ ሀ

ሀ.ታሪክን አይነግርም ለ. ሀዘንን ይገልፃል ሐ. ፈጠራን ያሳያል መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

3.ሀገረሰባዊ ክውን ጥበባት የምንላቸው---መ

ሀ. ሙዚቃ ዳንስ እና ድራማን ይይዛሉ ለ. ባህላዊ ተግባራት ናቸው ሐ. ከተውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋሉ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሃሰት በማለት መልሱ፡፡

1. የዶሮ ወጥ የኢትዮጵያ ባህላዊ ምግብ አይደለም፡፡ ሃሰት
2. ባህላዊ መድሀኒቶች አብዛኛውን ጊዜ ከእፅዋቶች ይሰራሉ፡፡ እውነት
3. ጥቁር መልበስ በአብዛኛው የአገራችን አካባቢ ደስታን የምንገልፅበት ልማዳችን ነው፡፡ ሃሰት
4. ጢያ ትክል ዲንጋይ በጉራጌ አካባቢ ይገኛል፡፡ እውነት

## 4.2 የዕይታና እደ ጥበባት አስፈሊጊነት በማህበረሰብ ውስጥ(4ክ/ጊዜ)

**የሚጠበቅ የመማር ውጤት**

ተማሪዎች ይህንን ት/ት ተመርው ካጠናቀቁ በኂላ፡-

- ስለ ዕይታና እደ ጥበባት ያላችሁን አመለካከት ያንፀባርቃሉ፡፡
- የዕይታና እደ ጥበባት አስፈላጊነት በማህበረሰብ ውስጥ ያለው ፋይዳ ይገልፃሉ፡፡
- ከሽክላ አፈር ጥቃቅን የሸክላ ውጤቶችንና ሐውልቶችን መስራት ይችላሉ፡፡
- ጥሩ የዕይታ ጥበብና የእጅ ስራዎች ክህሎቶችን ያዳብራሉ፡፡

- የዕይታ ጥበቦችን እና የእጅ ሥራዎችን ለልጆች በማስተዋወቅ እና በት/ቤቶች ውስጥ እንደዚህ ባሉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ በማድረግ የእውቀትና፣አካላዊ እና ማህበራዊ እድገታቸውን የመገንባት ትልቅ አቅም አለው ። በትምህርት ቤት ውስጥ የዕይታ ጥበብ እና የእደ ጥበብ ሥራዎች ጥቅሞች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 4.2.1. የዕይታና እደ ጥበባት አስፈሊጊነት በማህበረሰብ ውስጥ(4ክ/ጊዜ)

### አካላዊ ጥቅሞች

ጥሩ የዕይታ ጥበብ እና የእጅ ሥራዎች ክህሎቶችን ያዳብራሉ፡፡

አብዛኛዎቹ የዕይታ ጥበብ እና የእጅ ሥራዎች አእምሮ እና እጆችን ያካተቱ እንቅስቃሴዎች በመሆናቸው ጥሩ ክህሎቶችን ለማዳበር ይረዳሉ፡፡ በእርሳስ መንደፍ በቡሩሽ ቀለም መቀባት ያሉ ቀላል እርምጃዎች ጡንቻዎችን ለማጠንከር እና አእምሮ እድግትን ለማሻሻል ይረዳሉ፡፡

- ብልህነትን ያሻሽላል

የስነጥበብ እና የዕደ -ጥበብ ትምህርቶች የልጆችን ቅልጥፍና እና ጥሩ ክህሎቶችን ሊያሳድጉ ይችላሉ፡፡ተማሪዎች በእጅ ቅልጥፍና ብዙ ልምዶችን በማጎልበት የጥበብ ችሎታዎች ይጨምራል፡፡

ክፍል ሁለት፡- ገለጻ

- መምህር/ት የዕይታ -ጥበብ እና እደ ጥበብን በዝርዝር ያስረዱዋቸው እንዲሁም ባህልንናቅርሶችን እዲያደንቁ ታሪኮችን ያንቡላቸው፡የተለያዩ የቅርሳ ቅርሶችን አጫጭር ገለጻ አርጉላቸው፡፡

የዕይታ -ጥበብ እና በእደ ጥበብ አማካኝነት ተማሪዎች ባህሎቻቸው ፣ ቅርሶቻቸውን ዋጋ መስጠትና ማድነቅ ይማራሉ።ስለ ቅርስ ጥበቃም ይማራሉ። በዲዛይን፣በዕይታ-ጥበብ እና በእደ -ጥበብ ውስጥ ያለው ተሞክሮ በእራሳቸው ሥራ እና በሌሎች ላይ በጥልቀት እንዲያንፀባርቁ ያስችላቸዋል።ንድፍ አውጪዎች እንደ አርቲስቶች የፈጠራ ሀሰብን በመውሰድ ይሰራሉ ።

• ራስን መግለፅን ያሻሽላል

የዕይታ-ጥበብና በእደ -ጥበብ ውስጥ በመሳተፍ ፣ ተማሪዎች በፈጠራ ሥራዎቻቸው እራሳቸውን በአዎንታዊ እና ተጨባጭ ትርጉም ባለው መንገድ የመግለጽ ዕድል ያገኛሉ። በተጨማሪም የእይታጥበብ ሥራዎችን በራሳቸው ይሰራሉ።

• በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ያግዛል

ከሌሎች ተማሪዎች ጋር የዕይታ-ጥበብ ክፍል ውስጥ በጋራ መሳተፍ ሀሳቦቻቸውን ሲያካፍሉ ልጆች ከሌሎች ጋር እንዲገናኙ ዕድል ይሰጣቸዋል። የዕይታጥበብ እና የዕደ-ጥበብ ሂደትም የወላጅና ልጅ ትስስርን ያጠናክራል።

• በራስ መተማመንን ይጨምራል

የስነጥበብ እና የዕደ-ጥበብ እውቀቶች ጥቅም በተማሪዎች ላይ የስኬትና የኩራት ስሜትን ለማዳበር ይረዳሉ፣በራስ መተማመንን ያሳድጋሉ። መምህር/ት ተማሪዎች ፈጠራ ችሎታቸውን እዲያሳዩ ይዘዙዎቸው።

• ፈጠራን ያሻሽላል

አንድ ተማሪ የሚፈልገውን ሁሉ የመፍጠር እድሉ ፈጠራን ለማሳደግ ይረዳል።

• የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታን ያጎልብታል

አንድ ተማሪ የእይታ ጥበባት ትምህርት ችግሮችን በመጋፈጥ እና የመፍታት ትክክለኛ እና ውጤታማ ውሳኔዎችን ይማራል። ይህ ችግር ፈቺ አመለካከትን ለማዳበር ይረዳቸዋል።









ሥዕል፡-ተማሪ የእይታ ጥበባት ትምህርት

### 4.2.2 የእይታ ጥበባት ትምህርት የማስታወስ ችሎታ ያሻሽላል(4ክ/ጊዜ)

አንድ ልጅ በአዳዲስ ቀለሞች እና ቅርጾች በኪነጥበብ እና እደ ጥበባት ይማራል እንዲሁም ከተለያዩ ችሎታው እና ዘይቤዎች ጋር ይተዋወቃል። እንደ ሽመና መማር፣የሸክላሥራ ፣ወዘተ ያሉ እንቅስቃሴዎች ውስብስብ ንድፎችን በአዕምሯዊ እይታጥበብ በማስታወስ ይሰራሉ።



የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የሙዚቃ ጥበብ ሃሳብን ከውዝዋዜ እና ከትያትር ጥበባት ጋር ያለውን ዝምድና /አንድነት/እና ልዩነት ምን እንደሆነ በውይይት ያየንበትና ሦስቱንም የጥበብ ዘርፎች /ሙዚቃ፣ትያትርና ውዝዋዜ/የማይነጣጠሉና የአንዱ መኖር ለአንደኛው ውበት እንደሚሆን የዕይታ ጥበብ በማህበረሰቡ ውስጥ አስፈላጊና አካላዊ ጥቅም የማስታወስ ችሎታን እንደሚያሻሽል በግልፅ ተቀምጧል።

# ምዕራፍ አምስት

## ጥመርታ ዝምድናና ትግበራ (28ክ/ጊዜ)

### መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ በትኩረት የተገለጸውና በተግባር የተደገፈ አቀራረብ የሚታይበት ሲሆን በዋናነት ክ.ዕ.ጥ./የክወናና የዕይታ ትበባት/ከሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ጋር ያለውን ጥመርታ፣ ዝምድናና ትግበራ ላይ የሚያተኩር ሲሆን ዝርዝር ይዘቶቹ የትራፊክ፣ የኤች አይቪ. የአደንዛዥ ዕፅ ወዘተ… የሚገልፁ /ድንበር ተሻጋሪ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን ከመዝሙር /ከሙዚቃ/ ከውዝዋዜ፣ ከትያትር፣/ተውኔት/ እና የአካባቢው አቅጣጫ ማሳያ ምልክቶች/አርማ እና የተለጠፉ ማስታወቂያ ወይም ፖስተር፣ ቅድመ ዕይታ የንግድና ተዛማጅ ተዛማጅ ዘርፍ ያላቸው ድርጅቶች አርማዎች ስለ መንገድ ዳር የትራፊክ ጠቋሚ ምልክቶች በዝርዝር የተቀመጡበት ምዕራፍ ነው፡፡

አላማ

በዚህ ምዕራፍ በሙዚቃ ት/ት ጤንነትን ሊጎዱ ከሚችሉ ነገሮችን በቅድሚያ ራስን ብሎም ቤተሰብን፤ህብረተሰብን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ነገሮችን በዝርዝር እንዲያውቁ ማስቻል ነው።

## 5.1. የትራፉክ፣ የኤች አይ ቪ፣ የአደንዛዥ ዕፅ፣ ወዘተ... የሚገልፁ/ድንበር ተሻጋሪ ዘርፍ ብዙ ጉዳዮችን/፣ መዝሙራትን ማጣመ(6ክ/ጊዜ)

የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህን ት/ት ተምረው ከአጠናቀቁ ቦኃላ

- ከምንም በላይ ለጤንነታቸው ቅድሚያ መስጠትን ይረዳሉ
- ራሳቸውን ካላስፈላጊ አደጋ ይጠብቃሉ
- ወደአፍ የሚገቡና የማይገቡ ጎጂ ነገሮችን በሚገባ ያውቃሉ ይለያሉ

አጠቃላይ የመማር ማስተማር ስልቶች

- በቡድን ዝማሬ፣ በውዝዋዜ በተውኔት፣ስለ ዘርፈ ብዙ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች ይደረጋል
- ተማሪዎች ስለ ተፈጥሮ (ስለ ከዋክብት፣ ስለ ወንዝ፣ ስለ አእዋፋትወዘተ እንዲአምሩ ይደረጋል

የመማር መስተማር ማስተማሪያዎች

- የመለማመጃ ክፍሎች፣
- የሙዚቃና የቪዲዮ ማጫወቻ፤
- የአካባቢ የምት የሙዙቃ መሣሪያዎች ወዘተ....
- ምስሎች፤
- የምስል ማሳያና የድምፅ መስሚያ ግብዓቶች፤

ምዘናና ግምገማ

- ምልከታ
- የግል ፅብረቃ
- የቡድን ፅብረቃ
- ግለ ማህደር

አደጋ በአጋጣሚ በተወሰነ ቅፅበት ውስጥ ሊከሰት የሚችል ስለሆነ እራሳችንን ከአደጋው ለመከላከል የትራፊክ ደህንነት መርሆችን በሚገባ ማክበር ይጠበቅብናል ከነዚህም

- መንገድ ስናቋርጥ ግራና ቀኝ መመልከት
- ተደርቦ በቆመ መኪና ተከልሎ ለመሻገር አለመሞከር
- በእግረኛ ማቋረጫ መሻገር
- መኪና ላይ ከኋላ አለመንጠልጠል የመሳሰሉት ናቸው

አሽከርክር ረጋ ብለህ
ሁሌም ረጋ ብለን በትግስት እንንዳ
ሕይወት እንዳንቀጥፍ አካል እንዳንጎዳ x2 ከባድ
ሃላፊነት እንዳለብን አውቀን
ሁልጊዜም ስንንዝ ይሁን ተጠንቅቀን
መፍጠንና መቅደም አይደለም ችሎታ
ትግስት እንላመድ ሲኖረን እርጋታ
ሁሌም ረጋ ብለን በትግስት እንንዳ
ሕይወት እንዳንቀጥፍ አካል እንዳንጎዳ x2
ለእግረኛ ቅድሚያ እንስጥ በየመታጠፊያው
አደጋው ይቀንስ የሰው ህይወት መጥፊያው
ሴቶችና ህፃናት አረጋውይኑ
በመኪና አደጋ ከማለቅ ይዳኑ
አትቸኩል ረጋብለህ ረጋብለህ
አትቸኩል ትደርሳለህ ዘና ብለህ x2 ልጆችህን
አስብ ትዳርህን አስብ
ልጆችሽን አስቢ ትዳርሽን አስቢ x2
ሁሌም ረጋ ብለን በትግስት እንንዳ
ሕይወት እንዳንቀጥፍ አካል እንዳንጎዳ x2

እያሽከረከርን እንዳንዘናጋ

በቸልተኝነት ይደርሳል አደጋ

አይገኝምና ህይወት እንደዋዛ

መቼም ይሁን የትም ለህግ እንገዛ

ሁሌም ረጋ ብለን በትግስት እንንዳ

ሕይወት እንዳንቀጥፍ አካል እንዳንጎዳ x2

ከአልኮል ከአደንዛዥ ዕፅ ከሱስ ሁሉ ፀድተን

ድካም እናስወግድ በቂ እንቅልፍ አግኝተን

ፋታ ያጣ ሹፌር ሁሌም ይዘናጋል

ሰላማዊ ኑሮን በድንገት ይናጋል

አሽከርክር ረጋብለህ ረጋብለህ

አትቸኩል ትደርሳለህ ዘና ብለህ x2

ልጆችህን አስብ ትዳርህን አስብ

ልጆችሽን አስቢ ትዳርሽን አስቢ x2

የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ዜማውን በተደጋገሚ እነዲያዳምጡ ማድረግ
- ቃላቶቹን እንዲይዙ ማድረግ
- ሀረግ በሀረግ እንዲዘምሩ ማድረግ
- በቃላቸው ማዘመር

ኤች አይቪ ኤድስ

የሰውነትን የበሽታ መከላከያ በተለይ የነጭ ደም ሴሎችን (ህዋሳትን) በማጥቃት በቀላሉ ሰውነት ለበሽታ እንዲጋለጥ የሚያደርግ ቫይረስ ነው:: ኤችአይቪ የሚያጠቃው የሰውነት የነጭ የደም ሴሎችን የሰውነት የበሽታ የመከላከያ ተቋማትን ነው::ኤች አይቪ ቫይረሱ ከሰውንት ከወጣ ቦኃላ በጣም ደካማ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ አይቆይም ወድያውኑ ይሞታል:: በዚያ የተነሳ ነው ኤችአይቪ ከማንም ሰውጋር በምናደርጋቸው የዕለት እለት እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ፣ እንደ እጅ መጨባበጥ፣ መተቃቀፍ፣እና መሳሳም ሊያስተላልፉ እንደማይችሉና በተጨማሪም ኤች አይቪ በመጸዳጃ ቤት መቀመጫ፣በበር መኽፊቻ፣ በብርጭቆ መጠጫ፣ በምግብ ወይም በማንኛውም አይነት እንስሳ እንደ ቢንቢ ንክሻበመሳሰሉት ሊተላለፍ አይችልም::

የመማር ማስተማር ክንውኖች

- በርዕሱ ላይ የተሰሩ ሙዚቃዎች ያለውን ማለባበስ ይቅር የተሰኘውን ዜማ ማዘመር ክትትልና ግምገማ
- የመዝሙሩን ዜማና ግጥሙን መልእክት በሚገባ መረዳታቸውን መከታተል

አደንዛዥ ዕፅ

ጤንነትን ከሚያዛቡት ዋናው በአላስፈላጊ ሱስ መጠመድ ነው:: ሱስ በሁለት መንገድ ልንጠቃ እንችላለን::

በአፍ ወደ አካላችን የሚገቡ እንደጫት፣ሲጋራ ፣አልኮል መጠጦች አላስላጊየሆኑ እፆች ናቸው እነዚህ ንጥረ ነገሮች በአካላችን ውስጥ ሰርገው ሲገቡ በከፍተኛ ደረጃ አዕምሮን በመቀየር ጭንቀት ፣ጊዚያዊ ደስታ፣የስሜት መታወክ፣ የአዕምሮን መረጃ በማዛባት የመሳሰሉትን ከመፍጠራቸው ባሻገር የተክለ ሰውነት ቁመናን ያበላሻሉ፣፣ ይህን ተጠቃሚ ሰው በነርቭ፣ በጭንቀት ፣ሃይለኛ ራስምታት ፣በአጠቃላይ ራስን ለመግዛትም ሆነ ለመቆጣጠር አያስችልም ከሰውነት ጉዳት አልፎ በህይወት ላይ የሞት አደጋ ያስከትላል፣ ቤተሰብ ይበትናል፣ከስራ ላይና ከትምህርት ላይ መገለልን ያስከትላል ፣በርካታ ማህበራዊ ቀውሶችን ያስከትላል የዕፁ ተጠቃሚ የሚያሳያቸው ባህሪያት ድካም ፣እንቅልፍ ማጣት፣ግልፍተኝነት ከቤተሰብ መራቅ፣የአመጋገብ መዛባት፣ ገለልተኝነት

፤ገንዘብ ማባከን፤ ትኩረት ማነስ፤የማስተዋል ችግር፤ተስፋ መቁረጥ፤ጎልተው ይታይባቸዋል በዚህ በሽታ የተጠቁ ሰዎች አስፈላጊው ህክምና ከተደረገላቸው ወደቀድሞው ጤንነታቸው ይመለሳሉ፡፡

በአፍ የማይገቡ ሱሶች

- ቁማር አላስፈላጊ የገንዘብ የሃብት ብክነትን ከሚያስከትሉት ዋናው ነው
- ማህበራዊ ድህረ ገፅ በዚህ ሱስ ከሚያስከትሉት የጤና ችግር

መጨነቅ፤ድባቴ፤የትምህርት መከታተል መቀነስ፤ጠቃሚ የሆኑ ዕወቀቶችን ለማግኘት ምንባብን ማቋረጥ ናቸው

ቅድመ ጥንቃቄ

እረጋ ብሎ ማሽከርከር ፤ኤች አይቪን መከላከል ፤ጠንቅና እያለሳለሰ ስውን ከሰው በታች ከሚያደርገው ሱስ፤ መጠበቅ ቤተሰብን ከችግር ንብረትን ከውድመት የሀገር ኤኮኖሚን ከክስረት ማዳን ነው

የመማር ማስተማር ክንውኖች

- ስለ እፅ ጎጂነት በተለያዩ ምሳሌዎች መግለፅ
- ኤች አይቪ ለህፃናት መተላለፊያ መንገዶችነ በሚገባ ማብራራት
- ቴክኒዮሎጂ ውጤት ጠቃሚነትና ጎጂነቱን በሚገባ ማስረዳት

መልመጃ አንድ

ከዚህ በታች ለተሰጡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

1.የትራፊክ አደጋን ከሚያስከትሉት አንዱ ያልሆነው

ሀ.መረጋጋት ለ.ፍጥነት ሐ.ግራናቀኝ አለመመልከት መ.መንገድ መጣስ

2.አፍ የማይገባ ሱስ ከሚያስከትላቸው ጉዳቶች ውስጥ-------------------ነው፡፡

ሀ.የጊዜ ብክነት ለ.አንድ ቦታ መጠመድ ሐ.ጭንቀት መ ሁሉም

3. ሱስ የአእምሮ መዛባትን ያስከትለል ስንል

ሀ. ያለማሰብን ለ. መቆጣጠርን ሐ. መተውን መ. መ. የ

4.ኤች አይቪ በሽታ ይበልጥ የሚያጠቃው የሰውነት ክፍል

ሀ. አጥንት ለ. ነጭ የደምሴል ሐ. ልብ መ. አይን

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ሐሰት በማለት መልስ ስጡ

1. አረጋ ማለት የአዋቂነት የብስለት ውጤት ነው
2. ወደ አፍ የሚገባ ሱስ የፊት ገፅታን ከሚያበላሹት አንዱና ዋነኛው ነው
3. በእግረኛ ዜብራ መንገድ ማቋረጥ ህግን ማክበር ነው፡፡

አጠቃላይ የመማር ማስተማር ስልቶች

- የቡድንስራ
- ሰርቶማሰራት
- የተለማመዱትን ማሳየት
- ግልፅነት
- ማድመጥ

የመማር ማስተማር ማስተማሪያዎች

- የመለማመጃ ክፍሎች፣
- የሙዚቃና የቪዲዮ ማጫወቻ፤
- የምስል ማሳያና የድምፅ መስሚያ ግብዓቶች፤

መልስ

ምርጫ 1.ሀ 2. መ 3 . ለ 4 . ለ
1. እውነት 2. እውነት 3 . እውነት

### 5.1.1 የትራፊክ፣ የኤች አይ ቪ፣ የአደንዛዥ ዕፅ፣ ወዘተ... የሚገልፁ/ድንበር ተሻጋሪ ዘርፍ ብዘ ጉዳዮችን/ ውዝዋዜ ማጣመር(5ክ/ጊዜ)

ውዝዋዜ አስተማሪ በሆኑ በተለያዩ በሚዘጋጁ መድረኮች ላይ ከሙዚቃው ጎን ለጎን መልእክቶችን በክካል እንቅስቃሴ የሚተላለፍበት የጥበብ ዘርፍ ነው፡፡

አላማ

በውዝዋዜ ጤንነትን ሊጎዱ ከሚችሉ ነገሮችን በቅድሚያ መጠንቀቅ እንዳለብን ገላጭ መሆኑን ማሳወቅ

> የሚጠበቁ ውጤቶች
> ይህን ተምረው ከአጠናቀቁ ቦኃላ
>
> - ለጤንነታቸው ቅድሚያ መስጠትን ይረዳሉ

አጠቃላይ የመማር ማስተማር ስልቶች

- የቡድንስራ
- ሰርቶማሰራት
- የተለማመዱትን ማሳየት
- ግልፅነት

• ማድመጥ

የመማር ማስተማር ማስተማሪያዎች

- የመለማመጃ ክፍሎች፣
- የሙዚቃና የቪዱዮ ማጫወቻ፤
- የምስል ማሳያና የድምፅ መስሚያ ግብዓቶች፤

የውዝዋዜ መልእክት ገላጭነት

ውዝዋዜ የሀገር መልካም ገፅታን ገላጭ ከሆኑት ከባህል ክፍሎች መካከል አንዱ ነው ከዚህም አልፎ ለምሳሌ ስለ አንድነት ፤ትምህርት ማንበብና መፃፍ ፤ብሄር ብሄረሰቦች፤ስለግብርና ፤ወዘተ በመሳሰሉት መልእክት ገላጭ ነው፡፡

መማር ማስተማር ክንዋኔ

- የትራፊክ አደጋን ገላጭ አሽከርክር ረጋብለህ የሚለውን መዝሙር እስከ ውዝዋዜው መስራት
- ስለ ኤች አይቪ ኤድስ ኅብረ መዝሙርና ከመዝሙሩ እስከ ውዝዋዜው መስራት
- ሱስ ጎጂነት ገላጭ እንቅስቃሴ መስራት

ክትትልና ግምገማ

- በትክክል መዘመራቸውንና እንቅስቃሴውን በቡድን በማሰራት መከታተል

ውዝዋዜ ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጋር ግንኙነት ቢኖረውም ዋና ዋና የሚባሉት ግን የሚከተሉት ናቸው፡፡

ከሰውነት ማጎልመሻ ጋር፡- ውዝዋዜ የተለያዩ የአካል ክፍሎችን ማንቀሳቀስ ላይ መሰረት ተደርጎ የሚከወን ጥበብ ስለሆነና የተለያዩ አካላዊ ብቃት በመፈለጉ ብሎም አካላዊ ለውጥን ስለሚያመጣ ከስፖርት ሳይንስ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው፡፡

ከትያትር ጋር፡- ውዝዋዜ በትያትር ውስጥ አስፈላጊ የሆነና ልዩ ልዩ ክዋኔወች ላይ የሚንፀባረቅ ከመሆኑም ባሻገር በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ አብሮ የሚከወንና የማይነጣጠል ክወኔያዊ ጥበብ ነው፡፡

ከሙዚቃ ጋር፡- ሙዚቃና ውዝዋዜ የማይነጣጠሉ ክዋኔያዊ ጥበባት ሲሆኑ ሙዚቃ በመድረክ ላይ በሚቀርብበት ወቅት አብዛኛውን ጊዜ በውዝዋዜ የሚታጀብ ከመሆኑም በላይ ሙዚቃ ስሜትን ሲኮካና ቀልብን ሲገዛ በታዳሚው የሚከወን አካላዊ ምላሽ በመሆኑ ውዝዋዜ የሙዚቃ አንድ አካል ነው ቢባል የተጋነነ አይሆንም፡፡

ከስነ- ህይወት ጋር፡- ውዝዋዜን በመከወን ጤናን ለመጠበቅ ልዩ ጠቀሜታ ሲኖረው፤ የሰውነት ቅርፅን ለመጠበቅና አካልን ለማስተካከል፤ ውስጣዊ የሰውነት ስርዓትን ለማስተባበር፤ እንዲሁም አእምሯዊ ተዝናኖትን በመፍጠርና ጭንቀትን በማስወገድ በሚሰጠው ጥቅም ከስነ- ህይወት ትምህርት ጋር ጥምርታዊ ግንኙነት አለው፡፡

በለው፡ የእነሱ አህያ እየፈነጠዘች የኛን አህያ በግፍ ገደሏት፤ ወይኔ ሰውየው እውነታቸውን ነው ወንድ አጡብና በቁም ሞተናል!

ምን ግዴ፡ ይኸው የፈራሁት አልቀረም ነገ ደግሞ እኛን ያሸክሙናል ተው ያገሬ ወጣት ተነስ።

መርምር፡ አገራችን እኮ መሪ አላት የምን ግንፍል ግንፍል ነው ተረጋጉ ሳታጣሩ እሳት አትጫሩ።

አሸብር፡ እሱም ተላላኪ ከሀዲ ነው እንዳትሰሙት። ከፈለጋችሁ ከአሁን በፊት ከዳብን መሪ ጋር ተቃቅፎ የተነሳው ፎቶ ይሄውላችሁ።

አብላላው፡ አያችሁት ይሄን ጉድ እስቲ ፎቶውን ተመልከቱት ተቃቅፈው እየዶለቱ።

በለው፡ ይህ ጉዳይ ዘርን መሰረት ያደረገ ጥቃት ነው።

ምንግዴ፡ አያችሁት ሲዝት!

መርምር፡ ተው ይህ ጉዳይ ይጣራ?

አሸብር፡ አያችሁት ሲከላከልላቸው።

በለው፡ በቃ! ይበቃል ከዚህ በላይ ከመደፈር መሞት ይሻላል።

ምንግዴ፡ እና ሞክረና ባለጌ ደሞ ይዝታል እንዴ።

በለው፡ ይኸው አንዷን አህያ ሶስት አርገን ብድር መልሰናል።

ምንግዴ፡ እንዲያ ነው ነገሩ እንመጣልሃለን በተወለድንበት ትገነዛለህ።

አሸብር፡ እይዎት ምንግዴን መጣን እያለች ነው።

በለው፡ እና ማን ይፈራል ታዲያ ኑና ይለይልና።

አሸብር፡ የእነምንግዴ ማህበረሰብ ሰላሳ የበለውን ዘሮች ገደለ። (የውሸት ፎቶ ይለጥፋል።

በለው፡ ዝመት ህዝቤ ሆይ! ሚስትህ እየተደፈረች፣ ወንድሞችህ እየታረዱ፣ልጆችህ እየሞቱ ነው።

አሸብር፡ የእነበለው ብሄረሰብ የእነምንግዴን ዘር መቶ መቶ ገድለው ተበቅለዋል። (ፎቶ ይለጥፋል)

መርምር፡ ይህ ፎቶ የአሁን አይደለም። በድሮ ጊዜ ሌላ አገር የተፈጠረ ነው።

አሸብር፡ ውሸት አያችሁት ዘር ለማጥፋት አብሮ ሲደራጅ።

ምንግዴ፡ ጀግና ከሆናችሁ ይሄ ሬሳችሁ ኑና ቅበሩ።

አሸብር፡ እግዞ ተጨራረሱ ተመልከቱ አካባቢው ሁሉ በሬሳ ተሞልቷል።

ዳኘው፡ ተው የአገሬ ህዝቦች ለውጣችን የከነከናቸው የሚሰጡንን የእልቂት ሃሳብ ተው ለጥፋት አትመቻቹ።

አሸብር፡ እሱ የእነምንግዴ ዘር ስለሆነ አዘናግቶ የእነበለው ዘር ለማስጨረስ ነው።

በለው፡ አዎ ነቅተንበታል ኀበዝ እንዳታመነቱ አናት አናቱን ምቱ።
ምንግዴ፡ ተው ባክህ ወንበዴ የኔን ብሄር መቸም አታውቀውም እሽ።
መርምር፡ ካሁን በፊት የተፈጠረውን አስቡ ሌላ የጋራ ጠላት እየመጣብን ነው።
አብላላው፡ ሰበር መረጃ የእነበለውን ማህበረሰብ የሚረዱ የውጭ ሃይሎች መኖራቸው ተረጋገጠ።
ዳኘው፡ ይች የፀጋ ምደር ይኸ ለምለም አፈር፤
አላስከፋን ብሎ ባይፀናብን ችግር።
አገር እንዳንመራ፤
ሰርተን እንዳንከራ።
ተንኮል ጋርደውብን፤
እውነቱ ጠፍቶብን።
እሸሁን አንስተን፤
በራችንን ከፍተን፤
ለባዕዳን ሰጥተን፤
ባፈር ስንጫወት አቧራው በኖብን መች እኛ እናያለን፤
ጉድፍ እንደሚያወጣ እፍእፍ ስንባባል ጠፍተን እናልቃለን።
አለ ገጣሚው! ሰዎች በአህያ የጀመርነው የኅጠኝነት ችግር ከእንስሳት በታች እንድናስብ አድርጎናል።
በራችንን አጥረን አእምሯችንን አጥረን በሰፈር እንድንደራጅ አርጎናል።
መርምር፡ ልክ ነው ይህ ችግር ከሰፈር አልፎ የአገር ችግር ሆኗል። የተፈጠረውን ችግር ለሆዳቸው
ያደረጉ አወቅንልህ ባዮች ያልበላነውን እያስከፈሉን ነው።
ዳኘው፡ ከዛሬ ጀምሮ የእነአሸብር አይነት ተደብቀው የሚያጋድሉ ሆድ አምላኪዎች አገራችንን ሲበድሉ
እያየን መታገስ የለብንም።
በለው፡ ታሪክ ዳቦ ሆኖ አያውቅም እርምጃ ያስፈልጋል። ባለፈ ታሪክ ስንመራ አንኖርም።
መርምር፡ ታሪክማ ሊመራን ይገባል! ያለፈ ማንነታችን የነገ መንገዳችንን ያሳየናል። ካልሆነ ውሃ በሌለበት እሳት አውራ ነኝ ሊል ይችላል።
አሸብር፡ አጎንብሱ ልጫናችሁ እየተባልን መሆኑ ነው?
መርምር፡ ማንም ማንም ላይ አይጫንም ሁሉም በአገሩ እኩል መብት አለው ያ ማለት ግን አጥፊ
በዘር ተሸፍኖ ይኑር ማለት አይደለም፡

ምንግዴ፡ እኔ ምን አገባኝ ታዲያ ማንም ጫነ ተጫነ ዋናው ይመቸኝ፡፡

ዳኘው፡ ካሁን በኋላ አገርን አስቀድመን በህግ ጥላ ስር የመኖር ግዴታ አለብን፡፡

በለው፡ የቱ ህግ? ድንቄም ህግ አሉ! ህግ ቢኖርማ...

መርምር፡ አዎ የህግ ክፍተት ሊኖር ይችላል፤ ካሁን በኋላ ግን ክፍተቱን የሚሞላ የሚዲያም ሆነ ሌሎች ጉዳዮች የያዘ አዲስ ህግ መውጣቱን ሰምቻለሁ ካሁን በፊት ለነበረው ጥፋታችሁ ካሳ ይሆን ዘንድ ግን ሁላችሁም ተንበርክካችሁ ይቅርታ ጠይቁና ሰላም አውርዱ፡፡

(ሁሉም በመፀፀት ይቅርታ ይጠይቃሉ) ዳኘው፡ (በደስታ እየሳቀ) አሁን ሉላችሁም የሚሆን ዜና አለኝ የመጣብንን ችግር በጥበብና በትዕግስት አልፈነዋል፤ ጠላቶቻችንም አፍረዋል፡፡ ውጤታችን ያመጣውን ለውጥ ተከተሉኝና ላሳያችሁ፡፡ (ይከተሉታል፤ሰላማችንና አንድነታችን ለእድገታችን፤ አገር ከምንም ነገር በላይ ነው የሚል ፅሁፍ ያለበትና በአረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ የተለበጠ አዲስ ነገር ያሳያቸዋል፡፡ ሁሉም በደስታ ይተቃቀፋሉ)፡፡የኢትዮጵያ ብሄራዊ መዝሙር ይዘመራል፡፡

የማስተማር ስልት

- የቀረበውን ታሪክ አብራርተው እንዲናገሩ ማድረግ
- የገፀ- ባህርያትን ማንነትና ግንኙነት መስረዳት
- ታሪኩን አስፋፍተው እንዲፅፉ ማገዝ
- በቡድን መደረክ ላይ መለማመድ
- ቃለተውኔት እንዴት በቃል እንደሚያዝ ማሳየት
- ገፀ- ባህርያትን በደንብ እንዲወክሉ ማድረግ
- የገፅ ቅብ አልባሳትና ቁሳቁሶችን አጠቃቀም ማሳየት ያስፈልጋል፡፡

የማስተማሪያ ቁሳቁሶች

- ደረጃቸውን የሚመጥን ለመድረክና ለቪዲዮ የሚሆኑ አማራጭ ድርሰቶች፣
- ለመለማመጃ የሚሆን ሰፋ ያለ ክፍል፣
- እስክርቢቶ እና ወረቀት፣
- ቪዲዮ ካሜራ፣
- የመዋቢያ እና ገጽ ቅብ (ለመዋቢያ የሚሆን ዱቄት፤ ዋክስ፣ ፈሳሽ)፣
- ለተውኔቱ የሚስማማ አልባሳት፣

መልመጃ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሃሰት በማለት መልሱ፡፡

1. አብላላው ጥሩ ስነምግባር አለው፡፡ ሃሰት
2. መርምር ከአገር ዘርን ያስቀድማል፡፡ ሃሰት
3. አገር ከምንም ነገር በላይ ነው፡፡ እውነት

4. አሸብር ለሆዱ ያደረ በጥባጭ ነው። እውነት
5. ምንግዴ መወላወል አይታይባትም። ሃሰት
6. ዳኘው ጥበባዊ መሪ ነው። እውነት

### 5.1.2 አካባቢው አቅጣጫ ማሳያ ምልክቶች /አርማ እና የተለጠፋ ማስታወቂያ/ ፖስተር(3ክ/ጊዜ)

የሚጠበቅ የመማር ውጤት

ይህንን ክፍለ ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኂላ፡-

- የክወናና ዕይታጥበብ የትራፊክና የመንገድ ዳር አቅጣጫጠቃሚ ምልክቶች ትለያላችሁ።
- የክወናና ዕይታጥበብ ታዋቂ የሆኑ የሀገር ውስጥ የንግድና የአገልግሎት ሰጪ ምልክት አርማዎች ይተዋወቃሉ።
- የክወናና ዕይታጥበብ የተለመዱ ምልክቶችና አርማዎች ታውቃላችው።
- የክወናና ዕይታጥበብ የተለያዩ የፋሽን ልብሶች ማስታወቂያ ፓስተር የምግብና የመጠጥ መለያ አርማና ፖስተሮችን ይለያሉ።

ቅድመ ዕይታ

ስዕላዊ መግለጫ




ሥዕል፡-መረጃ ጠቋሚ ምልክቶች

አንዳንድየተለመዱ ምልክቶችና አርማዎች የሚከተሉት ናቸው
መምህር/ት ለተማሪዎች የሚከተሉትን የተለመዱ ምልክቶችን በተቀመጠው መሰረት በንባብና በምስል

- የልብ ምልክት - ፍቅርን፣ርህራሄን፣ይወክላል።
- የእርግብ ምልክት - ሰላምን ፍቅርን እና መረጋጋትን ይወክላል ።
- የሪቫን ምልክት - ሞትን እና ጥፋትን ይወክላል ።
- የዛፍ ምልክት - እድገትን፣ተፈጥሮን ፣ መረጋጋትን ዘላለማዊ ሕይወትን ይወክላል ።
- የጉጉት ምልክት - ምልክት ጥበብንና ብልህነትን ይወክላል።
- የቢራ ቢሮ ምልክት- ደግሞ መውደድን ፣ ውበትን እና ለውጥን ይወክላል ።
- የውሻ ምልክት - ታማኝነትን ፣ ጥበቃን ፣ ዳኝነትን ይወክላል ።
- የአንበሳ ምልክት - ድፍረትን፣ መሪነትን ፣ ንጉሳዊነትን ይወክላል ።
- የቀበሮ ምልክት - ተንኮልና ብልህነትን ይወክላል ።

በግራፊክ ዲዛይን እና በእውነተኛው ዓለም ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የተለመዱ ምልክቶች

- የቀስት ምልክቶች - አቅጣጫዎችን ለመወከል ያገለግላል
- ደመና ፣ ዝናብ፣ በረዶ እና የፀሐይ ምልክቶች - የአየር ሁኔታን ለመወከል ያገለግላሉ
- የኃይል፣ የዲስክ ፣ የዋይ ፋይ እና የብሉቱዝ ምልክቶች ቴክኖሎጂን ለመወከል ያገለግላል
- የተሽከርካሪ ወንበር - መረጃ ፣ የመታጠቢያ ቤት እና የማጨስ መከልከልን

የሚያመለክቱ ምልክቶች - ለሕዝብ ቦታዎች በተገኙ የተለያዩ ምልክቶች ላይ ጥቅም ላይ ውሏል።

## 5.2 - የንግድና ተዛማጅ ዘርፍ ያላቸው ድርጅቶች አርማዎች (ከ/2ክ/ጊዜ)

እነዚህን የእንስሳት ባህሪን ተከትለው የሰው ልጆች ለድርጅት አርማዎችን የንግድ ምልክቶች አድርጎ ሲጠቀሙባቸው ቆይቷል ። የንግድ ዘርፉ ያመረተውን ምርት የሚሰጠውን አገልግሎት ለደንበኞቻ ለማቅረብ ለማስተዋወቅ የንግድ ምልክት አርማ ዎችና መለያ ስሞችን ይጠቀማሉ ። ይህን ሀሳብ ግልፅ ለማድረግ በሀገራችን ብሎም በከተማችን የተለያዩ ምርትና የምርት መለያ አርማዎች ፤ ምልክቶች ከዚህ በታች እንመለከታለን ።

ታዋቂ የሆኑ የሀገር ውስጥ የንግድና የአገልግሎት ሰጪ ምልክት አርማዎች መካከል የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፣ አንበሳ ሻይ...... ...... ወዘተ ጥቂቶቹ ናቸው።

ሥዕል 1፡-የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አርማ

ሥዕል 2፡-የአዲስ አበባ ውሃ እና ፍሳሽ ባለስልጣን

ሥዕል 3 ፡-የኢትዮጵያ አየር መንገድ አርማ

### 5.2.1 - የትራፊክና የመንገድ ዳር አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች(2 ክ/ጊዜ)

የትራፊክ እና የመንገድ ዳር አቅጣጫ ጠቃሚ ምልክቶችን ስንመለከት ሁለት ወይም ሦስት ቀለማት ያልበለጡ በመጠቀም ለማህበረሰቡ በቀላሉ መረጃ እና ጥቆማ ይስጣሉ :: በአብዛኛው ጊዜ የመንገድ ዳር የትራፊክ ምልክቶችን በቀላሉ ማየትና ማስተዋል ይገባል :: ምልክቶችም አለም አቀፍ ናቸው ::







ሥዕል :-የትራፊክ እና የመንገድ ዳር አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች

**መልመጃ 1**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

1- የጉጉት ምልክት መገለጫ ጥቀሱ?

2- የሪቫን ምልክት ውክልና ግለጹ?

3- የዛፍ ምልክት ውክልና ግለጹ?

4- የልብ ምልክት ውክልና ግለጹ?

**መልስ:-** 1 ጥበብንና ብልህነትን ይወክላል፡፡

2-እድገትን፣ተፈጥሮን፣መረጋጋትን ይወክላል፡፡

3-ሞትን እና ጥፋትን ይወክላሉ

4-ፍቅርን፣ርህራሄን፣እና መናን ይወክላል፡፡

**መልመጃ 2**

ቀጥሎ በ‹‹ሀ›› ረድፍ የቀረቡ ምልክቶች ሲሆን በ‹‹ለ›› ረድፍ ከቀረቡት የአንቀጾቹ ዋና ዋና ሀሳቦች ጋር በማዛመድ መልሱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1-  | ሀ- አቅጣጫዎችን ለመወከል ያገለግላል |
| 2  | ለ- ይህም ሰላምን ፍቅርን እና መረጋጋትን ይወክላል |
| 3.  | ሐ-መኪና ማቆም ክልክል ነው |

**መልስ** ፡-1-ሐ 2- ለ 3 - ሀ

**መልመጃ 3፡-**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ፡፡

1- ታማኝነትን፣ጥበቃን፣ የሚወክለው የቱ ነው?

ሀ- ጅብ ለ- አንብሳ ሐ- ውሻ መ- ላም

2- በዕይታ ጥበብ የተገለጸው መውደድን ፣ ውበትን እና ለውጥን የሚወክለው ማን ነው?

ሀ- የአንብሳ ለ- የበረሮ ሐ-የውሻ መ- የቢራቢሮ

3- ድፍረትን፣ መሪነትን ፣ ንጉሳዊነትን የሚወክለው የቱ ነው?

ሀ- የቀበረሮ ለ- የአንበሳ ሐ- የቢራቢሮ መ- የጉጉት

**መልስ**፡- 1-ሐ 2-መ 3-ለ